# ክፍል ሶስት

# የዘር ማጥፋት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግና በዓለም ዓቀፍ ህግ ፡፡

## I. የዝር ማጥፋት ኮንቬንሽን (ዓለምአቀፍ ስምምነቶች) መግቢያ

እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ.ም. የተደረሠው ዓለምአቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል መከላከያና መቅጫ ስምምነትን በዋናነት ያተኮረው ወይም በፊት የነበሩትን ርዝራዥ ህጎች በጣም በተጠናከሩና ሃይል በተላበሡ ሕጎች እንዲቀየሩ ያስቻለው በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በነዚ /ጀርመን/ ሀይሎች በአንዳንድ ብሔሮች ፣ ዘሮች ፣የሃይማኖት ተከታዮች እና የእነዚህ ድጋፍ የሆኑ የፖለቲካ ሰዎች ላይ የደረሡ ኢ-ሠብዓዊ ጭፍጨፋ ነው፡፡ በወቅቱ የእንግሊዙ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት ዊንስተን ቸርቸል ይህንን ክስተት " ስም ልንሰጠው በማንችለው ወንጀል ነው በማለት ገልፀውት ነበር፡፡ አሥራ ዘጠኝ አንቀፃት ያሉት በ1948 ዓ.ም. የተደረሠው የዘር ማጥፋትን የሚከለክለውና የሚቀጣው ዓለም አቀፍ ስምምነት እ.አ.አ. በ1951 ዓ.ም. ተፈፃሚነት እንዲኖረው የተደረገ ሲሆን ሕጉም በማያሻማና ግልጽ በሆነ መልኩ የወንጀሉ ድርጊት የተፈፀመበትን ቦታ ወይም ሀገር ከግምት ሣያስገባ በአንድ ሕዝብ ፣ ብሔር ፣ጎሣ ፣ ዘር ፣ የሃይማኖት ተከታዮች ላይ የተፈፀመ እንደሆነ እንደ ዓለም አቀፋዊ የወንጀል ድርጊት እንደሚታይ ያስረዳል ወይም ይገልፃል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሀገሮች ይህንን ስምምነት ከማጽደቅ ባሻገር የሀገራቱን የወንጀል ሕግ አካል እንዲሆን አድርገዋል፡፡ ዘር ማጥፋትን በተመለከተ አባል ሃገሮች

ይህንን ስምምነት በፈፀሙበት ወይም በደረሡበት ወቅት ዓላማው በሰብአዊነት ላይ በየትኛውም የአለማችን ክፍሎች የሚፈፀሙ የወንጀል

ድርጊቶችን ለመከላከልና በተፈፀሙም ጊዜ የሚቀጣ ሕግ ለማውጣት የነበረ ቢሆንም አባል ሀገሮችም እሺታቸውን የገለፁ ቢሆንም በደንብ በተጠናከረ መልኩ ሕጉ ሥራ ላይ የዋለው ግን እ.ኤ.አ. ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ ነው። ዓለምአቀፍ ሕብረተሰብና መንግሥታቶች በዚህ ወቅት ሁለት ኢ-ሠብዓዊና አንገፍጋፊ ጭካኔ የተሞላበት የዘር ማጥፋት ወንጀሎችን ለማየት የተገደዱበት ወቅት ነበር ለማለት ይቻላል። አንደኛው በምዕራብ አውሮፓዊቷ ሃገር በሆነችው ዮጎዝላቪያ የደረሠው የዘር ማጥፋት ወንጀልን የተመለከተ ሲሆን ሌላው ደግሞ በአፍሪካዊቷ ሩዋንዳ የደረሠውን የዘር የማጥፋት ወንጀል ነው። ከነኚህ አሣዛኝ ክስተቶች በኋላ የዓለምአቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል ስምምነት ሕግ የወረቀት ላይ ግብር ከመሆን አልፎ አዎንታዊ ገጽታ በመላበስ ጊዜያዊ ዓለምአቀፍ ፍ/ቤቶች በማቋቋም ከላይ የተገለፁትን የዘር ማጥፋት ወንጀሎች የፈፀሙትን ግለሰቦች ወይም የመንግሥት አካሎች ለህግ በማቅረብ ዓለማቀፍ ሥምምነት ላይ ተደርሷል።

## የዘር ማጥፋት ትርጉም

በሁለተኛው የአለም ጦርነት ወቅት የደረሠውን ኢ-ሠብዓዊ ጭፍጨፋ በተመለከተ የወቅቱ የእንግሊዙ ሚኒስቴር የነበሩት ዊኒስተን ቸርችል ስም የለሹ ወንጀል በማለት ስም ያወጡለት ቢሆንም አሁን የያዘውን ቃል ዘር ማጥፋት / genocide / በማለት ስያሜ የሠጠው የአለም አቀፍ ሕግ ባለሙያ የሆነው ራፌል ሌምኪን ነው። እንደሌምኪን አተረጓጎምም የወንጀሉ ሠለባዎች ናቸው ተብለው የሚታሠቡት የሕብረተሰብ ክፍሎች የአንድ ሀገር ሕዝቦች ፣ ጎሣዎች ወይም የአንድ ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ማህበረሰቦችን የሚያጠቃልል እንደሆነ የሚያስረዳ መሆኑን ይገልፃል። የእንግሊዘኛው ቃል ጀኖሣይድ አመጣጡ ከግሪክ እና የላቲን ቃላቶችን በማዋሀድ የተፈጠረ ሲሆን / genos / ጀኖስ ማለት ዘር ወይም ጎሣን የሚያመለክት ሲሆን የላቲኑ / Caedo / መግደልን ያመለክታል። ሁለቱ ቃላቶችም በሚጣመሩበት ወቅት ከላይ በተጠቀሱት የሕብረተሰቡ ክፍሎች ላይ የሚደረጉ የመግደል ድርጊቶችን ያካተተ ስለመሆኑ የሚያስረዱ ናቸው በማለት ይገልፀዋል። ሌሞኪን ፅንስ ሀሣቡን ሲያስረዳ ፤

" የዘር ማጥፋት ወንጀል ድርጊት በዋናነት በግለሠቦች ላይ የሚያተኩር ሣይሆን በቡድኖች ወይም የሀይማኖት ተከታዮች ወይንም የአንድ አስተሳሰብ አራማጆች የሆኑትን የሕብረተሰብ ክፍል ለማጥቃት ታስቦ የሚፈፀም ወንጀል ነው፡፡ የወንጀል ድርጊቱን ፈፃሚው አካል የወንጀል ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመፈፀም ዓላማ ይዞ መንቀሣቀሱ መረጋገጥ ያለበት ለመሆኑ ሕጉ ያስረግጣል፡፡ "

ይህ ዓለም አቀፍ ስምምነት የዘር ማጥፋትን ወንጀል በትክክል ያልተረጎመ በማለት የሕግ ምሁራንና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ሂስ እየሠጡበት ያሉ ሲሆን ከዚህ ባሻገርም ሕጉ ተፈፃሚነት እንዲኖረው አስፈላጊው የሕግ ተርጓሚው ክፍል / አለመስተካከሉ / እንደ ችግር የሚታይ ነው ፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ይህ ዓለምአቀፍ ስምምነት የሚተችበት ነገር የተባበሩት መንግሥታት ባሳለፋቸው ሁለት ውሣኔዎች / ሪዞሉሽን / ላይ ተካተው የነበሩት የፖለቲካ እና የባህል ቡድኖችን አለማካተቱ ነው፡፡

ነገር ግን ብዙ ሀገሮች ለምሣሌ ኢትዮጵያ ፣ ፍራንስ ፣ ፖናማ ፣ ፖርቹጋል የመሣሠሉ ሀገራት በወንጀለኛ መቅጫ ሕጎቻቸው ውስጥ የፖለቲካ አራማጅ ቡድኖችን ያካተቱ ሲሆን በአንፃራዊ መልኩ ሌሎች ሀገራት በስምምነቱ ላይ በተደረሠው መሠረት የፖለቲካ ቡድኖችን አያካትቱም፡፡ አጠቃላይ በሆነ መልኩም የዘር ማጥፋት ወንጀል ድርጊት እ.ኤ.አ. በ1948 ዓ.ም. December 9 በተደረገው አለምአቀፍ ጉባኤ ስምምነት መሠረት ሲተረጎም የሚከተለውን / notion / መንፈስ የያዘ ለመሆኑ መረዳት ይቻላል፡፡

/1/ የዘር ማጥፋት ወንጀል አለ የምንለው በከፊል ሆነ በአጠቃላይ የአንድ ሀገር ሕዝብ ፣ ጎሣን፣ ዘርን ወይም የሀይማኖት ተከታዮች ክፍል ለማጥፋት በማሰብ የተደረገ ድርጊት ሲኖር ነው፡፡ እነኚህ ድርጊቶችም የሚከተሉት ናቸው ፤

1. የአንድ ቡድን ተከታዮችን መግደል
2. በአንድ ቡድን ተከታዮች ላይ አካላዊ ወይም አዕምሯዊ ጉዳት ማድረስ
3. የአንድ ቡድን ልጆችን ወደ ሌላ በማዘዋወር ባህልና አስተሣሠቡ እንዲቋረጥ ማድረግ፣

4. የዚህ ቡድን አባላት ዘር እንዳይስፋፋ በማሰብ ሆን ተብሎ ውልደትን ማቆም
5. የአንድን ቡድን ክፊል ወይም ሙሉ አካላዊ ውድመት እንዲያስከትል ሆን ተብሎ የሚደረግ የኑሮ ሁኔታ ማንደል፡፡

የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ሃሣባዊ ( mental element of the crime) እና ድርጊታዊ ክፍሎች የተሟሉ መሆን እንዳለባቸውም ያስገነዝባል፡፡ ሃሣባዊ ወንጀል ክፍሉ ተሟልቷል ለማለትም የድርጊቱ ፈፃሚዎች ከሚናዘዙት ይልቅ ድርጊቱ ሲፈፀም በነበረበት ወቅት የታዩ ወይም ከተከሠቱት ተጨባጭ ሁኔታዎች የወንጀሉ ፈፃሚዎች በዚያን ወቅት የነበራቸውን ሃሣብ በደንብ ያሣያል ተብሎ ግንዛቤ መውሰድ ይቻላል፡፡

## ቁሣዊ መገለጫ

የዘር ማጥፋት ወንጀል ቁሣዊ መገለጫ የሚባለው በወንጀሉ ፈፃሚዎች በግልጽ የተደረጉ ድርጊቶችን የሚያካትት በመሆኑ ለመለየት አዳጋች አይሆንም ፡፡ የዘር ማጥፋት ወንጀልን በተመለከተ የተደረሰው ዓለምአቀፍ ስምምነት እንደሚያመለክተው የአንድ የተወሰነ ሕብረተሰብ አባላትን መግደል ፤ በእነዚህ አካላት ላይ አካላዊና አዕምሮአዊ ጉዳት ማድረስ ፤ የአንድን ክፍል ሙሉ ወይም ክፊል አካላዊ ውድመት እንዲያስከትል ሆን ተብሎ የሚደረግ የኑሮ ሁኔታ በአንድ ቡድን ውስጥ ወሊድን ለመከላከል የታሰቡ ድርጊቶችን መፈፀም እንዲሁም የአንድን ቡድን ሕፃናት ወደ ሌላ ቡድን በግዳጅ ማዛወር የዘር ማጥፋት ወንጀል ቁሣዊ መገለጫዎች ናቸው፡፡

ነገር ግን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመሆን ምሉዕ መሆን የለበትም ፡፡ ምሉዕ ያልሆኑ ወንጀሎች ስንል በአንድ በተወሠነ የአዕምሮ / የአስተሳሰብ / ሁኔታ የተፈፀሙ ድርጊቶችን ለማመልከት ሲሆን እነዚህ ድርጊቶች እንደወንጀል ለመታየት የግድ የታሰቡት ጉዳቶች መድረስ አያስፈልጋቸውም፡፡ ከዚህም አኳያ የዘር ማጥፋትን በተመለከተ የተደረገው አለምአቀፍ ስምምነት በአንቀጽ 3 የዘር ማጥፋት ወንጀልን መፈፀም፣ ወንጀሉን ለመፈፀም ማሴር ፤ የዘር ማጥፋት

ወንጀል እንዲፈፀም በይፋ መቀስቀስና መምራት ፣ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመፈፀም መሞከር እንዲሁም የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈፀም መርዳት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ናቸው ብሎ አስቀምጧል። ከዚህ አንቀጽ መረዳት እንደሚቻለው አለምአቀፍ ማህበረሰብ የዘር ማጥፋት ወንጀል ከተፈፀመ በኋላ ከሚወሰዱ እርምጃዎች ይልቅ ወንጀሉ ከመፈፀሙ በፊት ሕጉ ጣልቃ እንዲገባና አጥፊዎችን እንዲቀጣ ይመርጣል ። ለምሣሌ ያህል በስምምነቱ መሠረት አንድን ቡድን ለማጥፋት ታስቦ የቡድኑን አባላት ለመግደል ማሴርና መስማማት አጥፊዎች ላይ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ በቂ ምክንያት ይሆናል። ሴራቸውን በተግባር እስኪያውሉና ያሠቡትን ጉዳት እስኪያደርሱ መጠበቅ አስፈላጊ አይሆንም።

# <u>የዘር ማጥፋት ወንጀል በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ</u>

አለማቀፍ የዘር ማጥፋት ወንጀል ስምምነት በሀገር ውስጥና በአለማቀፍ ደረጃ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመከላከል ያለመ ቢሆንም ይህንን ለማስከበር የተጠቀሙት ዘዴዎች ጠንካራ ያልነበሩና አለማቀፍ ማህበረሰብ በሀገሮች ላይ ሊያደርግ የሚችለው ጫና ላይ የተመሰረተ ነበር። ከዚህ መለስ ለቀድሞዋ ዩጎዝላቪያና ለሩዋንዳ የተቋቋሙት የወንጀል ፍርድ ቤቶች እንዲሁም አለማቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት አለማቀፍ የህግ ስርአት ያደረጉትን አስተዋፅኦ እና ስርአቱ ርእሰ መንግስታትን ጨምሮ ሌሎችንም ግለሰቦች እንዲታሰሩ ማድረጉን በባለፈው ክፍል አይተናል።

ምንም እንኳን የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመከላከል የፀደቀው አለማቀፍ ህግ እድገትና ይህንን ህግ ለማስከበር የተቀመጡት ዘዴዎች አስፈላጊ ቢሆኑም በአገሮች ውስጥ ይህንን አለማቀፍ ህግ ለማስፈፀም የሚቀመጡት ዘዴዎች ይበልጡን ወሳኝነት አላቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት አለማቀፍ ተቋማት በዚህ ህግ አፈፃፀም ላይ እንዲሳተፉ የሚያደርጉት የአንድ ሀገር የህግ ስርአት የዘር ማጥፋት ወንጀል የፈፀሙትን ጥፋተኞች ለመያዝና ለመቅጣት ያቃተው እንደሆነ ብቻ ስለሆነ ነው።

የአለማቀፍ ስምምነት አንቀፅ 5 እንደሚያትተው ሀገሮች ከራሳቸው ህገ መንግስት ጋር በተጣጣመ መልኩ የስምምነቱን ዓላማዎች ሊያሟሉ የሚችሉ የወንጀል ድንጋጌዎችን የማውጣትም ሀላፊነት ወስደዋል። የሀገር ውስጥ የማስፈፀሚያ ዘዴዎች በመጠን አነስተኛ የሆኑ የዘር ማጥፋይ ወንጀሎች ለመከላከል ብቻ የሚጠቅሙ ሲሆን በነዚህም ጊዜያት መንግስት የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም መሞከር፣ ለመፈፀም ማሴር፣ እና እንዲፈፀም ማነሳሳት በሚከለክሉ ህጎች በመታገዝ የዘር ማጥፋይ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ ገና ከጅምራቸው ሲከላከሉ ይታያሉ።

# የዘር ማጥፋት ወንጀል ትርጉም

በዘር ማጥፋይ ወንጀል ላይ የተደረሰው አለማቀፍ ስምምነት ወንጀሉን በተመለከተ ያስቀመጠው ትርጉም በመጀመሪያ በፕሮፌሰር ራፋኤል ሊምኪን በቀረበው እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባኤ በቀረበው ረቂቅ ስምምነት ላይ ከተቀመጠው ትርጉም በመጠን የጠበበ ነው። ይህም የሆነው የመጀመሪያው ረቂቅ የዘር ማጥፋት ወንጀል ሊፈፀምባቸው ከሚችሉት ቡድኖች መካከል የጋራ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ቡድኖች ሲያካትት በስተመጨረሻ የፀደቀው ስምምነት ግን እነዚህን ቡድኖች ከትርጓሜው ሳያካትት በዜግነት፣ በጎሳ በዘር በሀይማኖት አንድ የሆኑ ቡድኖችን ብቻ ተቀብሏል።

በኢትዮጵያ የወንጀል ህጉን የማርቀቁ ሂደት በቀዝቃዛው ጦርነት ከነበሩት ፖለቲካዊ እሳቤዎችና ተፅእኖዎች የፀዳ የነበረ ለመሆኑ የዘር ማጥፋይ ወንጀል ትርጓሜው ከዚህ ሰፋ ያለ ሆኗል። በመሆኑም የሀገራችንን ህግ እናያለን።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 269 የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲተረጎም በብሔር ፤ በብሔረሰብ ፤ በጎሣ ፤ በዘር ፤ በዜግነት ፤ በቀለም ፤ በሃይማኖት ወይም በፖለቲካ አንድ የሆነን ቡድን በመላ ወይም በከፊል ለማጥፋት በማሠብ የጥፋቱን ድርጊት ማደራጀት ትዕዛዝ መስጠት ወይም ድርጊቱን መፈጸም ሲሆን ፤

1. በማናቸውም ሁኔታ የማህበረሰቡን አባሎች የገደለ አካላዊ ወይም ህሊናዊ ጤንነት የጎዳ ፤ ወይም ህሊናዊ ጤንነት የጎዳ ፤ ወይም የአካል ጉዳት ያደረሰ ወይም ያጠፋ እንደሆነ ወይም ፤
2. የማህበረሰቡ አባላት በዘር እንዳይራቡ ወይም በህይወት እንዳይኖሩ ለማድረግ ማናቸውንም ዘዴ በሥራ ላይ ያዋለ እንደሆነ ወይም፤

3. የማህበረሰቡን አባላት ወይም ሕፃናት ግዴታ ከሥፍራ ወደ ሥፍራ ያዛወረ ወይም የበተነ ወይም ሊሞቱ ወይም ሊጠፉ በሚችሉበት የኑሮ ሁኔታ እንዲኖሩ ያደረገ እንደሆነ ፤

የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደተፈፀመ ይቆጠራል።

ይህ ትርጓሜ ለዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠሪዎች የሚሰጠው ከለላ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል። በቀድሚያ ይህ ትርጓሜ በዓለምአቀፍ ስምምነት ላይ የተቀመጡትን እና ግልጽ ያልሆኑ ሃሣቦችን በበለጠ ያብራራል። ለምሣሌ ያህልም " ድርጊት " የሚለውን ቃል ተንትኖ የማደራጀት ትዕዛዝ የመስጠት እና የመፈፀም ድርጊቶች እያለ የበለጠ በማብራራት የጥፋት ድርጊት የሚባለው ምን እንደሚያካትት እና እንደማያካትት በግልጽ አስቀምጦታል።

በሁለተኛ ደረጃም የሀገር ውስጥ ወንጀለኛ ሕጉ ከዓለምአቀፍ ስምምነት በተሻለ መልኩ "ለዘር ማጥፋት ወንጀል " የተሻለ ትርጓሜ ሰጥቷልለማለት የሚያስደፍረን ነጥብ በሕጉ ከለላ ስፋት የበዙ ቡድኖችን መብት ያካተተ በመሆኑ ነው። ለምሣሌነትም ብሔር ፤ ብሔረሰቦች ፤ የቀለምና የሃይማኖት ቡድኖች በሕጉ ጥላ ስር ከለላ ከተሠጣቸው ውስጥ ይካተታሉ። በመሆኑም የኢትዮጵያ ወንጀል ሕግ ከዓለምአቀፍ ስምምነት በተሻለ መልኩ ብዙ ቡድኖችና አባላቶቹ ከጥቃት የሚታደግ ነው ለማለት ያስደፍራል።

በስተመጨረሻም ሕጉ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ የአንድ ፖለቲካ ቡድን አባሎችን የህጉ ከለላ ከሚያስፈልጋቸው ቡድኖች መካከል እንዲፈረጁ ያደረገ ሲሆን ይህንንም ለማድረጉ ምክንያት የእነዚህ ፖለቲካ አራማጅ ቡድኖች ተጠቂነት ከሌላ ዓይነት ቡድን ልዩነት የሌለው መሆኑን በማመን ነው።

## የዘር ማጥፋት ወንጀል አላባዎች (Elements of Genocide)

የዘር ማጥፋት አላባዎች ከሆኑት ሁለት ነገሮች መካከል አንደኛው ወንጀሉን ለመፈፀም ያለው የሀሳብ ክፍል ወይም በእንግሊዝኛው አጠራር (the mens rea) ሲሆን ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ በህግ የተከለከለውና የሚያስቀጣው የወንጀሉ ድርጊት በእርግጥ ተፈፅሞ ሲገኝ ነው። የዘር ማጥፋት ወንጀል በተመለከተ ከተደረገው ስምምነት ጋር ተመሳሳይ የሚያደርገው የዘር ማጥፋት ወንጀልን ተፈፅሟል ለማለት ከሚያስፈልገው ሀሳባዊ ክፍል ሁለት ንዑስ ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነሱም 1ኛ የመንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የተቃጣባቸው አንድ ቡድን እና አባላቶቹ ላይ መሆን እንዳለበትና እነዚህም ቡድኖች ወይም አባላቶች የሚጋሩት የጋራ የሆነ መለያ ሊኖራቸው እንደሚገባ ያስቀምጣል።

ሁለተኛው ንዑስ ክፍል ደግሞ እነዚህን ቡድኖች ወይም የቡድኑን አባላት

በከፊል ወይም በሙሉ የማጥፋት ዘመቻ የተደረገ ለመሆኑ መረጋገጥ ያለበት ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳል። በአጠቃላይ በሁለቱ ትርጉሞች መካከል ያለው ልዩነት / ሃሳባዊ ክፍሉን በተመለከተ / የሰፋት ብቻ ነው። ሀገራቶች በውስጥ ህጋቸው ውስጥ ከዚህ ህግ አኳያ መብታቸው እንዲጠበቅ የተደረጉ ቡድኖች ከዓለም አቀፍ ስምምነት ጋር በምናስተያየው ጊዜ በቁጥር በዛ ያለ ነው። ቁሣዊ መገለጫውንም በተመለከተ ሀገራቶቹ በውስጥ ሕጋቸው በዛ ያሉ ድርጊቶችን እንደ ዘር ማጥፋት ድርጊት አድርገው ሲያስቀምጡ ይታያሉ። ከዚህ በተጨማሪም ለየት ባለ መልኩ አባል ሃገራቶች በውስጥ ሕጋቸው ላይ ጥርት ባለና በማያሻማ መልኩ የወንጀሉ ቁሣዊ መገለጫ የሆነውን ድርጊት ያስቀመጡ ሆነው ይገኛሉ። ለምሣሌ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፀመ ፣ ተሞከረ ፣ ለመፈፀም አስማማ ፣ ሲፈፀም ያገዘ ፣ የሚሉትን ነገሮች በግልጽ እንዳስቀመጠ ለማየት ይቻላል።

## ወንጀሉ ተፈፀመ የተባለው መቼ ነው ?

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ እንደሚያስቀምጠው ወይም እንደሚተረጉመው የዘር ማጥፋት ወንጀል የአንድን ቡድን አባላት መግደል ወይም በሰውነታቸው ላይ ጉዳት ማድረስን እና የመሣሠሉትን በዝርዝር የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በተመለከተ የመሠናዳት ድርጊቱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ የሠጡ ወይም ድርጊቱ ሲፈፀም የተሣተፉ ሰዎችን በወንጀለኛነት ያስቀምጣል፡፡

ስለዚህ እነዚህ መብታቸው በሕግ የተጠበቀላቸውና ድርጊቱም በሚፈፀምበት ጊዜ እንደዘር ማጥፋት ሊቆጠር የሚያስችሉ በዝርዝር የተቀመጡ ድርጊቶች በተፈፀሙ ጊዜ የዘር ማጥፋት ተፈጽሟል ለማለት ያስችለናል፡፡ በመሆኑ ሰው የመግደል ወይም አካል የማጉደል ድርጊት ሲፈፀም ወይም እንደዚህ ዓይነት ድርጊቶች እንዲፈፀሙ ያደራጀ ወይም ትዕዛዝ የሠጠ ሲሆንና ድርጊቱም የሚፈፀመው በአንድ የፖለቲካ አስተሳሰብ የሚያራምዱ አባሎች ላይ በተፈፀመ ጊዜ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን እንደ አንድ ራሱን የቻለ ምሣሌ ልናስቀምጥ እንችላለን፡፡ በመጨረሻም የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፀመ ለማለት የግል የቡድኑ አባላቶች ሙሉ በሙሉ ከምድረገጽ መደምሰስ አስፈላጊ አይሆንም፡፡ በከልል ወይም ከድርጊቱ አፈፃፀም አኳያ ይህ ነገር በአጭሩ ሃሣባዊ እና ቁሣዊ የወንጀሉን ክፍሎች አሟልቶ የተገኘ ከሆነ ብቻ በቂ እንደሆነ ህጉ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

## የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም የሚደረግ ሙከራ

የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመፈፀም የሚደረግ ሙከራ ወንጀሉ በእርግጥ ቢፈፀም የሚያስከትለውን ዓይነት ቅጣት እንደሚያስከትል ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ማለትም ቁሣዊ የወንጀል ክፍሉ ወይም ድርጊቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ነባራዊና ተጨባጭ ሁኔታ አለመፈፀም ወይም መፈፀም አለመቻል የድርጊቱን ፈፃሚ ከወንጀል ተጠያቂነት ነፃ አያደርገውም፡፡ ለምሣሌ እንደግለሰብ እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ተከታዮቹን ወይም ቡድን ለማጥፋት ሀሣብ በመያዝ አጠገቡ ከሚኖረው ጎረቤት ይህን የወንጀል ድርጊት መፈፀም

ቢጀምርና በፖሊስ ቢያዝ የግቡ ከዳር አለመድረስ ከዘር ማጥፋት ወንጀል ተጠያቂነት አያድነውም፡፡

## የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም የሚደረግ ሴራና እቅድ

ሰዎች በግላቸው በአዕምሮአቸው ውስጥ የትኛውንም ዓይነት "መጥፎ ሆነ ጥሩ " ሀሣቦችን ለማሰላሰልና ለማሰብ መብት የተሰጣቸው ቢሆንም ይህንን ዓይነት ሀሣብ ማለትም የወንጀል ድርጊትን ለመፈፀም ከሚያስችሉት የሀሣብ ክፍል ጋር ተመሣሣይ በሆነ መልኩ ከራሣቸው አልፎ ከሌላ ሶስተኛ ወገን ጋር የወንጀል ድርጊትን ለመፈፀም መመሣጠር፣ ድርጊቱን ለመፈፀም የመሰናዳት ዝግጅት ለማድረግ የሚጥሩ ግለሰቦችን ግን ይህን ክልል በመጣስ መብታቸው በሕግ በተጠበቀ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ የሚደረግን የወንጀል ድርጊት እንዲፈጽሙ ሕጉ አያዝዛቸውም፡፡

## ቅስቀሣና ይፋዊ የሕዝብ መነሣሣት ድርጊቶች

ከላይ ከተገለፀው በተለየ መልኩ በግለሰብ ደረጃም ሆነ ሕዝብን የዚህ ዓይነት የዘር ማጥፋት ወንጀል ለመፈፀም በገንዘብ፣ በስጦታዎች ፣ በማስፈራራት ፣ በማስገደድና የመሣሠሉትን በመጠቀም ይህ ሁኔታ እንዲከሰት በቃል ፣ በስዕል ወይም በጽሁፍ ያስተላለፈ በወንጀሉ ይጠየቃል፡፡

## ወንጀሉ እንዲፈፀም ያገዘ

አንድ ሰው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንዲፈጽም አግዟል የሚባለው ይህን አይነቱን የወንጀል ድርጊት እንዲፈጽም ሀሣቡ ወይም ፍላጎቱ ኖሮት የወንጀል ድርጊት በሚፈጽምበት ጊዜ ወይም ከዚያን ጊዜ በፊትና በኋላ እርዳታውን በማንኛውም አይነት መልኩ የሠጠን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ እርዳታው መረጃ መስጠትና ፣ ሀሣብ ማካፈልን፣ ቁሣዊ እርዳታዎችን መስገስና የመሣሠሉትን ያጠቃልላል፡፡